# *ትኩረት*

## ቁ * 5

## የወያኔ/መለስ ወደ ገቦች አስከፊ ድራማ በዳላስ ቴክሳስ

"ያም ሲያማ፤ ያም ሲያማ ወገኔ፤ ለኔ ብለህ ስማ"

የዛሬ አራት አመት ገደማ ነው ወያኔ የምርጫ 97 ሕዝባዊ ሰላማዊ ድል በሽብር ለውጦ ከባህር ገብታ የወጣች ድመት የሚመስል ያክል ደንግጦና በርግጎ ዳግም የሰራትል ስህተት ላይደግም በቁርጥ ታጥቆ የተነሳው። ከምርጫው ማግስት በመቶ ሺህወች አሰረ። በደቡብ፣ በሰሜን፤ በመሀል የማጎሪያ ጣቢያወች ከፈተ concentration comp እንደሚሉት ማለት ነው። መቸምውንም ዘረኝነት በሕዝብ ትግል ካልተወገደ እድገቱ ፋሽስት መሆን ነው። አወ ይህ አዲስ the new world order የሚሉት የአንድ ልእለ ሐይል የበላይነት፤ በከፊልም ቢሆን ከቀዝቃዛው ጦርነት በተሻለ የመንግስታቱ ተጠያቂ የመሆን ጅማሮ፣ ከሞቡቱ፣ ኤዲያሚን፣ መንግስቱ፣ አይነት መሪወች በኋላ የመጣው ወይም ከድሕረ ርዋንዳና ብሩንዲ የሕዝብ ፍጅት በህዋላ የተቋቋመው ያለማቀፍ ፍርድ ቤት በመጠኑም መንቀሳቀስ መጀመር ባይኖር ኖሮ። ወይንም መለስና ይህ ዘረኛ መንግስቱ በቀዝቃዛው ጦርነት ወይም ከዚያ በፊት የተከሰቱ ቢሆን፡ ሊያጋጥመን ይችል የነበረው አንድ ትውልድን መተረ ከምንለው የደርግ/ኢሰፓ ሥርአት የከፋ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። አወ ዘረኝነት ፋሽስትነት ነው። ለተለየ አስተሳሰብ ብቻ ቦታ መንፈግ ሳይሆን። ከጸጉር እስከ እግር ጥፍር ወይም ከቋንቋ እስከ መንደር እኔን ያልመሰለ ሁሉ ጠላት ባይ ነው።

(ሕወሐት) ወያኔ ሐርነት ትግራይ ሲፈጠር አላማየ ብሎ የተነሳው ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ (ነጻ አውጥቶ ይሉታል) እራሷን የቻለች አገር መመስረት ነበር። ለዚያ በዋና ጠላትነት የሚፈርጀው አንዴ አማራ፡ ሌላ ጊዜ የሸዋ፡ ብዙውን ኢትዮጵያ በሚል መተክል በመሆኑ። ጥላቻውም ሆነ ጠላትነቱ ለገዥወች ወይም ለተወሰነ መደብ ወይም ለስርአት እንዳልነበር እንረዳለን።

ይህ የተምታታበት ዘረኛ ድርጅት በትግል ባሳለፋቸው አመታት ከቀኝ ግራ እየተላጋ በለስ ቀንቶት አንዲስ አበባ እስኪገባ የኔ የሚለው ስርአተ አስተዳደር ያልነበረው በጭፍን የትግራይ የሚለውን ሰንደቅ አንጠልጥሎ ሌላው ሁሉ ጠላቴ ነው ብሎ ያመነ አስካሁንም ከ18 አመት ግዛት በኋላ አላማውን ያልቀየረ ነውረኛ ጉድ ነው።

ምርጫ 97 ማንነቱን እንደገና እንዲገልጥ አስገደደውና ፈቅዶ የተሰለፈበትን ሕዝበ ውሳኔ አልቀበልም ካለና የቁጣ ፋሽታዊ አሸባሪ በትሩን ባስታጠቀው ያጋዚ ሰራዊት ካፈነ በሕዋላ ይሁነኝ ብሎ የተያያዘው የከፈታቸውን ቀዳዳወች መሙላት ነበር።

በዚህ ጉዞው በዋነኛ ጠላትነት የመዘገበውን በውጭ የሚኖረውን ዜጋ በቻለው ሁሉ ለመግጠም ያለ የሌለ ነዋዩን አፈሰሰ። ተዘጋጀ። የውጭ አጋዦቹን አስተባብሮ የራሱን ካድሬወችም እንዲሁ አሰልጥኖና 51 ገጽ የስራ መመሪያ አሸክሞ ወደውጭ አዘመታቸው።

አንዳንድ ወገኖች ብዙወቻችን ማለት ይቻላል በነጻ አገር የሚኖር ዜጋ ሁሉ ለዚህ ብኩን አሸባሪ መንግስት ይደለላል ብለን ስለማንገምት ሳናስብ ሳናልም እንቅልፍ አጦ በሚሰራ ደመኛና ለግል ኑሮ ብለው ማነኛውንም ስብእናቸውን ለመሸጥ በተዘጋጁ ግለሰቦች ለመወረር በቅተናል።

**በዳላስ የተከሰተው አሳዛኝ የወያኔ ዘመቻ፡**

እስኪ አስቀድመን ስለዳላስ ትንሽ እንበል። በ1991 ባገራችን የተከሰተው የዘር ፓለቲካና ጎጠኝነት በዳላስ ያልታየ ነበር። ወገን ባንድ ቤተክርስቲያን በአንድ መስጊድ በአንድ ኮሚውኒቲ ማህበር ተሰባስቦ ተገናኝቶ ጎጥም ሆነ ቋንቋ ሳይለየው የኖረ። በውጭ ለሚኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ ተምሳሌ የነበር አካባቢ ነው። አልፎ ተርፎ ኤርትራ የምትባል አገር እንኳን ከተከሰተች ወዲህ፤ የዚያ አካባቢ ተወላጆች በክፉ በደጉ ከቀሪ ወገናቸው ሳይለዩ የኖርንበት አካባቢ ነው። ዛሬም ቢሆን የበለጠ ማህበራዊ ትስስሩ እንዳለ የቀጠለ ቢሆንም። ይህ አንድነታችን ያስቀናው ጠባብ ቡድን ለመልካም ስራ ተምሳሌ እንዳንሆን ላለፉት ፲፫ አመታት የደከመበት ዛሬ እውን ሊሆን መቀራቡን ስናይ በአስገራሚ ነው።

ላለፉት አራት አመታት ወያኔ በውጭ በከፈተው ዘመቻ አንዱ ተጠቂ በመሆን ላይ ያለው የዳላስ ኢትዮጵያውያን ነን። መጀመሪያ በመስጊድና በቤተክርስቲያናችን መጡብን በተለይ በቅዱስ ሚካኤል ላይ የተከፈተው ዘመቻ የቀጠለ ሲሆን አሁን ደግሞ በግልጽ ወጥተው ኮሚውኒቲአችን በሚገለገልበት ሬዲዮ ጣቢያ የዳላስ ሕዝብን ለወያኔ ተቀጥላ ለሆነ ባ.አ.ዴ.ን ለተባለ ድርጅት ስር ለማሰባሰብ እየተሞከረ ነው።

**የዚህ ጸያፍ ደባ አጀማመር፡**

በትኩረት ቁ፡ ፪ እንዳሳየነው፡

የወያኔ/ኢሕአዴግ አባላት በ2007 እና 2008 ተንቀሳቅሰው ያደራጁት አንድ ስብስብ ዛሬ አድጎ ንዋይ ያባዘናቸው እንኳን የራስን ስብእና የወለዱትን ልጅ ለመለውጥ የተዘጋጁ ሰውችን ቀልብ ስቦ በይፋ ወደወያኔ ጎራ እንዲቀላቀሉ ሆነ።

ህላዊ ዮሴፍ የተባለው የባ.አ.ዴ.ን አመራር አባል በመጣበት ወቅት የዳላስ ኢትዮጵያውያን እስከ ስብሰባ በጠራበት አዳራሽ በመገኘት ያሰበውና ተላላኪወቹ የገቡለት ቃል ሳይሆን። አገር ወዳዱ ልኩን ነግሮ ስብሰባው በታሰበው ሳይቀጥል የታሰበለትን ግብም እንዳይመታ ሆኖ በሕዝብ ፕሮቴስት ተበትኗል። በጊዜው ፫ የዳልስ ፓሊስ (squad cars) ከውጭ፤ ሁለት ፓሊሶች ከስብሰባው አዳራሽ በመቆም ሕዝቡን አንድ በአንድ እየተቆጣጠሩ አስገብተው ሦስት ዎገኖችን ግን እንዳይገቡ

በፖሊስ ቢታገዱም ከውጥ የገባው ባንድነት ሆ ብሎ በመጮህ እንዲገቡ ሆኗል። በፖሊስ ሀይል ስብሰባ ጨርሰን እንወጣለን ያሉት ወዶገቦችና የወያኔው መንግስት አባላት ያሰቡት ሳይሳካ ተበትኗል።

በማግስቱ እንደሰማነው ህላዊ ዮሴፍ፣ የወያኔ አንባሳደር በዮኤስ፣ እና በግዜው ያማራ ክልል አስተዳዳሪ ተብየው የተወሰኑ ተስፈኞችን በመሰብሰብ አንድ Ethio-American consensus committee የተባለ በውጭ ለወያኔ የሚሰራ ኮሚቴ በድብቅ በግል ቤት ባደረጉት ስብሰባ ተቋቋመ ብለው አስነግረዋል።

ይህ ኮሚቴ ከተመሰረተ በኋላ በእርግጥም ብዙ የማይናቁ ተግባራትን አከናውኗል። የሩቅ አላማ አድርጎ የተነሳው አመታትን አስቆጥረው የተገነቡ የማህበረሰቡን ተቋማት በቁጥጥር ስር ማዋል ነው። ያን ለማድረግ መጀመሪያ ማፍረስ እንደሆነ ታምኖበታል በወያኔ ማለት ነው። ለማፍረስ እየተወሰዱ ያሉ እርምጃወች።

1- የእምነት ቦታወችን ሲሆን በማግባባት በወያኔው የፖለቲካ ተሿሚ አቡነ ጳውሎስ ስር ማዋል።

2- ያሊሆን አልቻለም ፕላን ሁለት መተዳደሪያ ደንቡን መቀየር።

3- ያም ተሞክሮ አልተቻለም። በመሆኑ ሌላ ቤተክርስቲያን መክፈት እና ለማህል አገር ሰው አቡነ ተክለሐይማኖት ታቦትን ማስምጣት። ለሰሜኑ ወገናችን ቀልብ እንዲስብ የተዘየደው አቡነ አረጋዊን በአንድ ቤ/ክ ውስጥ ማድረግ ነበር። አወ ይህ አዲስ በካሊፎርኒያ አገረ ስብከት (የወያኔው ሊቀጳጳስ)ተሿሚ ማለት ነው ተመርቆ የተከፈተ ቤ/ክ የታሰበውን ያክል በዳላስ አማኒያን ተቀባይነት ሊያገኝ አልቻለም። እንዲያውም ሌላ ቀርቶ የትግሪኛ ተናጋሪ ወገኖቻችንን አስባለሁ ብሎ ያሰበው ቁስ ያም ያልተሳካ ሆኖ ቀረ። ይህ ሳይሳካ በመቅረቱና የተከፈተው ቤት ክርስቲያን ትቂት ቅጥረኛ አባላትን ብቻ በማፍራቱ፦

4- ሌላና ዋነኛ አማራጭ ያሉት ቅ/ሚካኤል/ቤተክርስቲያንን መክሰስ ነበር። አወ የመጀመሪያው ክስ በቂ አይደለም ተብሎ ፋይል ተዘጋ፣ ሁለተኛ ይግባኝ አሉ፣ ያም እንዲሁ ያለበቂ ምክንያት በመሆኑ ፍርድቤቱ ይህንም ዘጋው። አሁን ሌላ ክስ መጥሪያ ለቤተ/ክ ደርሶታል። በእርግጠኝነት ለመናገር ይህም ቢሆን እጣው ያው ቢሆንም። ቅጥረኞች ምእመኑን በገንዘብ አዳክመው ለመውሰድ በመነሳሳታቸው ፍልሚያው ይቀጥላል።

ከላይ የዘረዘርናቸውን ሙከራ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት ልብወለድ ያለመሆናቸውን የዳላስ ነዋሪ ያውቃል። ሆኖም ቅጥረኞች የዞሩባቸው ሙከራወች ሁሉ አለመስራታቸው ቢታወቅ፤ ሰሞኑን በግልጽ ወጥተው በኮሚውኒቲ ማህበራችን አስርገው ባስገቡት አንድ ግለሰብ አማካኝነት <u>“ በምህጻረ ቃሉ አ.ል.ማ በዝርዝር ስሙ አማራ ልማት ማህበር” የተባለ ድርጅት በዳላስ መደራጀቱንና አላማና ተግባሩ በመንግስት ፈቃድ (በወያኔ) ማለት ነው እየተካሄደ ባለው ልማት ተካፋይ እንዲሆን ጥሪ በማቅረብ ላይ ናቸው።</u> ግለሰቦቹ ማለትም ለወያኔ ለመስራት ታጥቀው የተነሱት የዘረኛው መንግስት

አጋር የሆኑት አንድ ኤንጅነር፣ ሌላው ዶክተር ሲሆኑ ከመሀላቸው ኑሮ ያልከፋባቸው አልጠግብ ባዮችም መኖራቸውን ተረድተናል። ይህ አስከፊ ተግባራቸውን እስካላቀሙ ድረስ ዝርዝር ስማቸውን የምናወጣ መሆኑን እንገልጻለን።

በማጠቃለያ ይህ በዳላስ ነዋሪ ስደተኛ ዜጋ ላይ እየተካሄደ ያለው የመለስ መንግስት አስከፊ ተግባር በየትም ቦታ ለመጀመሩ መጠራጠር አንችልም። ዛሬ በሳይበር ሚዲያ የሚካሄደው የወያኔ ቅጥረኞች ስራ ለዚያ አካባቢ ልምዱ ያላቸው የሚያውቁት ነው።

በሰሞኑ በቤን ሬዲዮ ቃለ መጠይቅ የቀረበለት መለስ ዜናዊ እንዳለው የምርጫ 1997 ክፍተቶችን ለመዝጋት ያለመታከት ሰርተናል ነበር ያለው። ይህ ምላሹ ለኛ ዳላስ ነዋሪ ለሆን ኢትዮጵያውያን በተግባር ያየነው በመሆኑ አላስገረመንም። ሆኖም ደግሞ በዚህ የተከሰቱ ችግሮች በኛ ኮሚውኒቲ ብቻ ተወስነው ያሉ ባለመሆናቸው ሁሉም ዜጋ ጠንቅቅ ቢል መልካም ነው እንላለን።

EthioLion.Com